## መመሪያ ቁጥር 812/2013

## የፌደራል ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም እና ተግባርና ኃላፊነቱን እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 171(2) በተሰጠ ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   መመሪያው "የፌደራል ቋሚ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም እና ተግባርና ኃላፊነትን እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 812/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

   1. **"አዋጅ"** ማለት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ነው፡፡
   2. **"የፌደራል አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ"** ማለት ሚኒስትሩ የተቀናጀ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ሥርዓት በማቋቋም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን

## Directive No 812/2021

## Directive on the Re establishment and assigning Duties and Responsibilities of permanent Federal Labour Advisory Board

This Directive has been issued on the basis of the authority vested on the Ministry of Labour and Social Affairs by Proclamation No.1156/2019, Article 171(2).

## Part One

## General

1. **Short Title**

   This Directive may be cited as"Re establishment and assigning Duties and Responsibilities of permanent Federal Labour Advisory Board". Directive No 812/2021.

2. **Definitions**

   In this Regulation unless the context provides otherwise,

   1. **"Proclamation"** means Labour Proclamation 1156/2019.
   2. **"Federal Labour Advisory Board"** is a tri-lateral body that advise in preparation and amendment of laws and policies on Labour relations by establishing a (coordinated) Labour administration

ለማዘጋጀት፣ ለማስተባበር፣ ለመከታተልና ለማስፈፀም፤ የሥራ ሥምሪት አገልግሎትና የሥራ ሁኔታ መቆጣጠሪያ አገልግሎት ለማጠናከር በሚሰጠው አመራርና የማስተባበር ኃላፊነት ዙሪያ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ምክር እንዲሰጥ የተቋቋመ የሦስትዮሽ አካል ነው፡፡

3. **"አግባብነት ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች"** ማለት ከመንግሥት ከተሠጣቸው ተግባርና ኃላፊነት አኳያ ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አፈፃፀም የሥራ ቅርበት አላቸው ተብሎ ሲታመን የአማካሪ ቦርድ አባላት እንዲወክሉ በሚኒስትር የሚመረጡ የፌዴራል መንግሥት ተቋማት ናቸው፡፡
4. **"የአሠሪ ኮንፌዴሬሽን"** ማለት በአገር አቀፍ ደረጃ ተቋቁሞ የተመዘገበ አብላጫ አባላት የሚወክል የአሠሪ ፌዴሬሽኖች ህብረት ነው፡፡
5. **"የሠራተኛ ኮንፌዴሬሽን"** ማለት በአገር አቀፍ ደረጃ ተቋቁሞ የተመዘገበ አብላጫ አባልነት የሚወክል የሠራተኛ ፌዴሬሽኖች ህብረት ነው፡፡
6. በአዋጁ አንቀፅ 2 ሥር የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
7. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

system in the Ministry, as well as advise, strengthen, guide, coordinate, and inspect employment services of work conditions.

3. **"Appropriate government offices"** are institutions of the federal government assigned by the Minister to represent Board members, as they are considered to be familiar with the implementation of the Labour Proclamation on account of their official duties and responsibilities.
4. "**Employers' Confederation**" means a registered Association established at national level, comprised of Employers' Federations representing majority of Employers.
5. "**Workers' Confederation**" means a registered Union established at national level, comprised of Workers' Federations and representing majority of Workers.
6. The definitions in Article 2 of the proclamation apply to this Directive.
7. Provisions of this directive set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን፣</u>

ይህ መመሪያ በመንግሥት፣ በአሠሪዎች እና በሠራተኞች መካከል በሚከናወኑ የማህበራዊ ምክክር ጉዳዮችና በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚኖሩ ግንኙነቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3. **Scope of Application**

This Directive shall be applicable in social dialogue discussions that are held between government, employers and workers as well as relations between employers and workers.

## ክፍል ሁለት

## የፌዴራል ቋሚ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ስለማቋቋም፣

## Part Two

## Establishment of a Federal Labour Advisory Board

4. <u>መቋቋም</u>

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "አማካሪ ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) አሠሪና ሠራተኛን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሚኒስትሩን የሚያማክር የሦስትዮሽ አካል ሆኖ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

4. **Establishment**

The Labour Advisory Board herewith established as one of a tri-lateral body and called "Advisory Board", shall hold consultative discussions on matters related to employers and workers and make recommendations to the Minister.

5. <u>የአማካሪ ቦርድ ዓላማ</u>

ውጤታማ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ስርዓት ከማጠናከር አኳያ አሠሪና ሠራተኞች ከመንግስት ጋር ተቀራርበው በመመካከር ለመስራት የሚያስችል አሳታፊ የሆነ የሶስትዮሽ የምክክር ስርዓት ለመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡

5. **Objective**

The objective of the Advisory Board is to put in place an effective and participatory tri-lateral consultative Labour administration system that enables employers and workers to work closely with the government.

6. <u>የአማካሪ ቦርዱ የማማከር ተግባርና ኃላፊነት፣</u>

አማካሪ ቦርዱ፡-

1. በሥራ ላይ ባሉ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በሚመለከቱ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣

6. **Duties and Responsibilities of the Advisory Board**

The Advisory Board;

1. The Board shall submit, for the

ደንቦች እና መመሪያዎች አፈፃፀምና በነዚሁ ላይ ሊኖር ስለሚገባው ማሻሻያ፣ ማስተካከያ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ተጠንተው በሚቀርቡ አዳዲስ የፖሊሲ፣ የሕግ፣ የደንብና የመመሪያ ረቂቅ ማሻሻያዎች ላይ በመወያየት አስተያየት ይሰጣል፣

Minister's consideration, ideas for the amendment of existing laws, policies, regulations, and directives, as well as drafts of new ones.

2. አጠቃላይ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት ስለሚስፋፋበት እና ሥራ አጥነትን ደረጃ በደረጃ ለመቀነስ ስለሚቻልበት ሁኔታ በሚቀርቡ ሪፖርቶችና ማብራሪያዎች ላይ በመምከር አስተያየት ይሰጣል፣

2. The Board shall consider reports and elaborate suggestions on how to expand employment services opportunities and reduce unemployment.

3. የአገር ውስጥ የሥራ ሥምሪት አገልግሎትን በማስፋፋትና በማጠናከር ሂደት በኤጀንሲዎች አሠራርና በሠራተኞች መብት አጠባበቅ ዙሪያ ለሚነሱ ችግሮች የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፣

3. The Board shall discuss reports and suggest solutions towards expanding employment services by strengthening the operational process between agencies and the safeguarding of workers' rights.

4. በውጭ ሃገር የሥራ ሥምሪት የኤጀንሲ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ቁጥጥር እና በውል ማፅደቅ ዙሪያ ሊነሱ በሚችሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በጥናት ተደግፎ በሚቀርብ ሪፖርት ላይ በመምከር የማስተካከያ እርምጃ ስለሚወሰድበት ሁኔታ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል።

4. The Board shall discuss reports and consider remedial measures to be taken, in the licensing, supervision, contract confirmation of foreign employment agencies (agents).

5. የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፍቃድ አሰጣጥ፣ አፈፃፀምና የቁጥጥር ሂደት ከመልካም አስተዳደር ጉድለት የፀዳ ሆኖ አሠራሩ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማምጣት በሚያስችል መልኩ እየተሠራ ስለመሆኑ በሚቀርብ ሪፖርት ላይ በመወያየት ምክር ይሰጣል፣
6. አጠቃላይ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ሥርዓት ስለሚጠናከርበትና የኢንዱስትሪ ሠላም ሰፍኖ ምርታማነት ስለሚያድግበት እንዲሁም በሥራ ቦታ የሁለትዮሽ ማህበራዊ ምክክር ሊዳብር ስለሚችልበት ሁኔታ ስለተሠራው ሥራ ያለውን አፈፃፀም አስመልክቶ በሚቀርብ ሪፖርት ላይ በመወያየት ሃሳብ ይሰጣል፤
7. የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተጠብቆ የሥራ ሁኔታዎች ስለሚሻሻሉበትና የተለያዩ የሙያ ጠንቆች ስለሚወገዱበት ሁኔታ እየተሠራ ስላለው ሥራ ተወያይቶ ምክር ይሰጣል፣
8. በሥራ ቦታ የሚከሰቱ አደጋዎችን ለመቀነስ መወሰድ ስላለባቸው ዝርዝር የመከላከያ እርምጃዎች አፈፃፀም በሚቀርብ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ አስተያየት ይሰጣል፤
9. ሃገራዊ የኢኮኖሚ ልማት ግቦችን ለማሳካትና ኢንዱስትሪውን ለማዘመን

5. The Board shall discuss reports and offer advice on the granting and regulating of work permits to foreign nationals in order to ensure that it is free from maladministration and enables knowledge and technology transfer.
6. The Board shall discuss reports and advise on the strengthening of Labour administration as well as on the promotion of industrial peace and social dialogue between employers and workers.
7. The Board shall discuss occupational safety and health and advise on the improvement of work conditions, and on the removal of impediments.
8. The Board shall discuss reports in detail on the reduction of occupational accidents and on preventive measures to be taken to reduce them.
9. The Board shall offer advice to the Minister on how to coordinate and strengthen cooperation between the

በሴክተር ደረጃ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፣ አዋጁን በሚያስፈፅሙ ባለድርሻ አካላትና በልማት አጋሮች መካከል ሊዘረጋ ስለሚገባው የቅንጅትና የትብብር አሠራሮች ስለሚጠናከርበት ሁኔታ ሚኒስትርን ያማክራል፤

Ministry entrusted with modern industrial sector implementing national development goals, and stakeholders, and development partners.

10. በሥራ ቦታ ፆታዊ ጥቃትና ወሲባዊ ትንኮሳን እንዲሁም የኤች.አይ.ቪ. ኤድስንና የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ከመከላከል አንፃር በሚቀርቡ ልዩ የአፈፃጸም ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ ምክር ይሰጣል፤

10. The Board shall deliberate on reports regarding sexual offenses and harassment in the workplace as well as HIV aids and exploitation of child Labour and advise on their prevention.

11. የአካል ጉዳተኞች፣የሴቶች እና ወጣቶች የሥራ ሁኔታ ለማስጠበቅ የተሰሩ ስራዎችን አስመልክቶ በሚቀርብ ሪፖርት ላይ በመወያየት ሀሳብ ይሰጣል፤

11. The Board shall discuss reports and advise on measures taken to protect the working condition of disabled, women's and young workers.

12. አጠቃላይ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በተመለከቱ የመረጃ አሰባሰብ፣አደረጃጀት እና አጠቃቀም ዙሪያ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ለመገንባት እየተሠራ ስላለው ሥራ በሚቀርብ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ አስተያየት ይሰጣል፤

12. The Board shall deliberate on reports regarding the gathering, organizing and utilization of data, and on current efforts to build a data management system on Labour relations, and offer its considered recommendations.

13. በኢትዮጵያ የፀደቁ የዓለም የሥራ ድርጅት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን አፈፃፀም ከመከታተል አንፃር እንዲሁም በመንግሥት እንዲፀድቁ ሊመከርባቸው በሚገቡ አዳዲስ ዓለም አቀፍ

13. The Board shall follow up on the implementation of ILO agreements ratified by Ethiopia, and also study reports on new proposed international agreements, and offer its advice to the Minister.

ስምምነቶችን አስመልክቶ በሚቀርቡ ጥናቶች ላይ ተወያይቶ ሃሳብ ይሰጣል፤

14. አዋጁን መሠረት ባደረጉና ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ሌሎች ጉዳዮች በአጀንዳ መልክ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት ተገቢውን ውይይት በማድረግ ሚኒስትርን ሊያማክር ይችላል፡፡

15. እንደ አስፈላጊነቱ በተለየ ሁኔታ ሊታዩ የሚገባቸው የኢኮኖሚ፣ የጤና፣ የትምህርትና የሙያ ሥልጠና ጉዳዮችን የተመለከቱ የጥናት ሪፖርቶች ሲቀርቡ ባለሙያዎች በቦርዱ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ሙያዊ ማብራሪያ እንዲሰጡ ለመጠየቅ ይችላል፤ በቴክኒካል ኮሚቴዎች የጥናት ውጤት የተመለከተ ሪፖርት ላይም ተወያይቶ ምክር ይሰጣል፤

16. የመወያያ አጀንዳዎችን ያፀድቃል፣ ሌሎች ተጨማሪ አጀንዳዎች እንዲያዙ ሃሳብ በማቅረብ ውይይት ያካሂዳል፣ በደረሰበት ጭብጥ ላይም ሚኒስትርን ያማክራል፣

17. የቦርዱን ዓመታዊ የሥራ እቅድና መርሐ-ግብርን መርምሮ ያፀድቃል፤ አፈፃፀሙን በመከታተል ለጽ/ቤቱ ትዕዛዝ ይሰጣል፣

14. The Board shall advise the Minister on agendas submitted to it that are based on the Proclamation regarding Labour and related matters.

15. The Board may invite experts to its meeting to elaborate on matters related to the economy, health, education, and vocational training as well as to offer advice on training and study reports of technical committees.

16. The Board approves the agenda, holds discussion on including additional matters, and then advises the Minister on the substantial brief.

17. The Board examines and approves the annual plan and program, and directs the office of Advisory Board to follow up on its implementation.

18. የአማካሪ ቦርድ አባላት በተናጠልም ሆነ በአንድነት በሚያካብቱት ልምድ በተገኘ የመልካም ተሞክሮ ልውውጥ ላይ በመወያየት የጋራ መግባባት በተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ለሚኒስትር ሃሳብ ማቅረብ ይችላሉ፤

19. አማካሪ በርዱ የራሱ የውስጥ አሠራር ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

7. <u>**የአማካሪ ቦርድ አባላት፤**</u>

1. የአማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ይሆናል፡፡
2. ከመንግሥት ሚኒስቴር መ/ቤቱን በመወከል የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታን እና አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የሚወከሉ 5 ተወካዮች፤
3. ከአሠሪ ኮንፌዴሬሽን የሚወከሉ 5 ተወካዮች፤እና
4. ከሠራተኛ ኮንፌዴሬሽን የሚወከሉ 5 ተወካዮች ያሉት ነው፡፡

8. <u>**የአማካሪ ቦርድ ሰብሳቢ ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት**</u>

የአማካሪ ቦርድ ሰብሳቢ የቦርዱን ሥራ ለመምራት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የየወቅቱ አጀንዳዎችን ለቦርዱ

18. Board members may submit proposals to the Minister regarding matters upon which they have reached consensus as a result of a fruitful exchange among themselves about their individual or collective experiences.

19. The Advisory Board may issue its own internal rules, and procedure.

7. <u>**Advisory Board members**</u>

1. The Minister of Labour and Social Affairs shall be the chairperson of the Advisory Board.
2. The State Minister of Labour Affairs, by representing the Ministry, and five members representing appropriate government offices .
3. Five representatives from the Confederation of Employers.
4. Five representatives from the Confederation of workers.

8. <u>**Duties and Responsibilities of the Chairperson of the Advisory Board**</u>

The chairperson of the Board shall have the following duties and responsibilities.

1. The chairperson presents the agenda for

በመግለፅና እንዲፀድቁ በማድረግ የቦርዱን ስብሰባዎች ይመራል፣

2. በቴክኒካል ኮሚቴዎች ለሚካሄዱ ጥናቶች አስፈላጊው የፋይናንስ ምንጭ ሊገኝ የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋል፣

3. የአማካሪ ቦርዱን ሥራ የሚመዝንበትና የሚከታተልበትን መንገድ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋል፣ከአማካሪ ቦርዱ የተሰጡ አስተያየቶችን ለሥራው እንዲያመቸው መዝግቦ ይይዛል፣

4. እንዳስፈላጊነቱ የአማካሪ ቦርዱን ሥራ አስመልክቶ በተናጠልም ሆነ ከቦርድ አባላት ጋር በመሆን መግለጫ ሊሰጥ ይችላል፣

5. የአማካሪ ቦርዱን የሥራ እቅድና የአፈፃፀም መርሐ-ግብር ለቦርዶ አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

6. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታን ሊወክል ይችላል፣

7. አግባብነት ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር እንደአግባቡ እያጠና ሊቀይር ይችላል፡፡

8. አማካሪ ቦርዱ የራሱ የሆነ የውስጥ አሠራር ሥነ ሥርዓት እንዲኖረው ሲያስፈልግ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ በማድረግ በአማካሪ ቦርዱ ውይይት ተካሂዶበት እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

approval, and presides over the Board's meetings.

2. The chairperson looks for financial sources to fund studies to be conducted by technical committees.

3. The chairperson looks for ways to assess and follow up on the Board's activities, and keeps records of the Board's deliberations and recommendations.

4. The chairperson, singly or together with Board members, may make public statements about the activities of the Board whenever it is necessary to do so.

5. The chairperson presents the Board's action plan and program to the Board for its approval.

6. The chairperson may delegate the State Minister of Labour Affairs, when he is not available for a Board meeting.

7. The chairperson may alter the list of appropriate authorities on the basis of appropriate studies conducted.

8. The chairperson presents to the Board, for discussion and eventual approval, the Board's internal operational procedure.

9. <u>ስለ አማካሪ ቦርድ ዋና ፀሐፊ</u>

የአማካሪ ቦርዱ ከአሠሪ እና ከሠራተኛ ወገን መካከል በየሁለት ዓመቱ በየተራ የሚመረጥ ዋና ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡

10. <u>የቦርድ ዋና ፀሐፊ</u> <u>ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የአማካሪ ቦርዱ ዋና ፀሐፊ ተጠሪነቱ ለቦርድ ሰብሳቢ ሆኖ የቦርዱን የስብሰባ አጀንዳና ቃለ-ጉባኤ መያዙን ያረጋግጣል፡፡
2. የአማካሪ ቦርድ ስብሰባ ለማካሄድ የስብሰባ ጥሪ ደብዳቤ ላይ ይፈርማል፡፡
3. የቦርድ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና አፈፃፀም ሪፖርት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፡፡
4. የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ሥራ ይከታተላል፡፡
5. በአማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## <u>ስለ አማካሪ ቦርድ ጽሕፈት ቤት</u>

11. <u>የአማካሪ ቦርድ ጽሕፈት ቤት</u>

1. አማካሪ ቦርዱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውስጥ የራሱ ቢሮ ኖሮት በአስፈላጊ የሰው

**9. <u>The Secretary of the Advisory Board</u>**

The Advisory Board shall elect a secretary every two years, alternately from the employers, and from the workers.

**10. <u>Duties and Responsibilities of the Secretary of the Board</u>**

1. The Board's secretary, accountable to the chairperson of the Board, shall ensure that the agenda and minutes of meetings of the Board are kept properly.
2. The secretary signs on the invitation letter to hold the meetings of the Advisory Board.
3. The secretary ensures that the implementation report on the Board's annual work plan is prepared.
4. The secretary follows up on the work of the technical committees.
5. The secretary performs all other tasks assigned to her/him by the Advisory Board.

## Part three

## <u>The secretariat Office of Advisory Board</u>

**11. <u>The Office of the Advisory Board</u>**

1. The Advisory Board shall have its own fully staffed office within the premises of

ኃይል የተሟላ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

2. የአማካሪ ቦርዱ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነቱ ለሚኒስትር ሆኖ በአንድ የጽህፈት ቤት ኃላፊ ይመራል፡፡

12. **<u>የአማካሪ ቦርድ ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የአማካሪ ቦርድ ጽሕፈት ቤት፦

1. ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ እንዲሁም አፈፃፀም ሪፖርቶች ለአማካሪ ቦርድ ቀርበው ምክክር ከተደረገባቸው በኋላ ቃለ-ጉባኤዎች ተዘጋጅተውና በአባላቱ ተፈርመው በመረጃነት እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

2. ስብሰባ ከመካሄዱ አስቀድሞ ለመነጋገሪያ የሚሆኑ አጀንዳ ጉዳዮችን ከዕቅድ በመለየት ለአማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ አቅርቦ ያስፀድቃል፣ የቦርድ ስብሰባ የሚካሄድበትን ቀንና ሰዓት እንዲወሰን ሃሳብ ያቀርባል፡፡

3. ለአማካሪ ቦርድ አባላት መላክ ያለባቸው የመወያያ አጀንዳዎችና ሰነዶች እንዲዘጋጁ በማድረግ በየአድራሻቸው በደብዳቤ እንዲላክ ያደርጋል፤ መደረሱንም ተከታትሎ ያረጋግጣል፡፡

the Minister of Labour and Social Affairs.

2. Office of the Advisory Board will be accountable to the Minister of Labour and Social Affairs, and shall be headed by Head of the office.

12. **<u>Duties and Responsibilities of Advisory Board Office</u>**

Advisory Board office shall have the following duties:

1. The Advisory Board shall deliberate discussion minutes on policies, laws, international agreements, regulations, directives and implementation reports, and ensure that minutes of meetings are kept and signed.

2. The office shall highlight agenda items, distinguish them from the plans and present them to the Board Chairman for approval, as well as propose the dates and hours for the Board’s meeting.

3. The office shall send the agenda and relevant documents to the addresses of the members of the Advisory Board, and ensure that they have been received.

4. የማህበራዊ ምክክር ሥርዓትን ለማስፋፋትና ሰላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት እንዲሰፍን በአማካሪ ቦርዱ መታየት ባለባቸው አሠሪና ሠራተኛን የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለሰብሳቢው ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በዕቅድ እንዲካተት ያደርጋል፡፡

5. የአማካሪ ቦርድ አባላት በተለያየ ምክንያት ሲጓደሉ ክትትል በማድረግ በወቅቱ እንዲሟሉ ለማድረግ አስፈላጊውን ይፈፅማል፣

6. የአማካሪ ቦርዱና የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት በቦርዱ ታይቶ እንዲፀድቅ ያደርጋል፤

7. በአማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፡፡

**13. <u>ስለ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተግባርና ሀላፊነት፡-</u>**

1. ከአማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ በሚሰጥ ትዕዛዝ መሠረት የጽህፈት ቤት ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል ይቆጣጠራል በተጨማሪም የአማካሪ ቦርዱን ሥራ ለማሳካት ያልተቋረጠ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1)

4. In order to promote social dialogue and industrial peace, the office shall suggest to the Board matters for deliberation, and upon approval it shall have them incorporated into the plan.

5. The office shall do whatever is necessary in order to fill the quorum when some Board members are not able to attend.

6. The office prepares the Advisory Board's annual plan and submits it for approval by the Board.

7. The office performs other additional tasks assigned to it by the chairperson of the Board.

**13. <u>Duties and Responsibilities of the Head of the Office</u>**

1. The Head shall exert every effort to coordinate, carry out, and supervise tasks assigned by the chairperson.

2. Notwithstanding the general provision of sub-Article 1 of this Article, the Head shall:

አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የጽሕፈት ቤቱ ሀላፊ፡-

ሀ. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13 የተመለከቱትን ጽሕፈት ቤት ተግባር እና ሀላፊነት ሥራ ላይ ያውላል፡፡

ለ. በአማካሪ ቦርድ እና በጽህፈት ቤቱ ለተከናወኑ ተግባራት ወቅታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ያቀርባል፤

ሐ. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ የአላቂና የቋሚ እቃዎች ግዥ ፍላጎት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

መ. የቦርዱ ጽህፈት ቤት ተግባራት በብቃት ለማከናወን በአስፈላጊው የሰው ሃይል እንዲሟላ ለሰብሳቢው ሃሳብ ያቀርባል፣

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. የመተባበር ግዴታ

የአሠሪ እና የሠራተኛ ኮንፌዴሬሽን፣ አግባብነት ያላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና የአማካሪ ቦርድ አባላት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ

a. perform the duties and responsibilities indicated in Article 13 of this Directive.

b. prepare timely implementation reports on the work of the Advisory Board and the Office.

c. prepare the list of consumer and capital goods that need to be bought for the Office, and shall have them purchased upon approval.

d. shall propose the human resource needs for the efficient implementation of the tasks of the office of the Board.

## Part Four

## Miscellaneous Provisions

### 14. Duty to Cooperate

The Confederations of Employers and workers, appropriate government offices and members of the Advisory Board have the duty to cooperate in the implementation of

አለባቸው፡፡

this Directive.

15. ***የተሻረ መመሪያ***

*የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድን ለማቋቋም ጥቅምት 17 ቀን 1997 ዓ.ም. የወጣው መመሪያ ተሽሯል፡፡*

**15. Repealed Directive**

The Directive to establish the Labour Advisory Board issued on October 17/1997 is here by repealed.

16. ***መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ***

*ይህ መመሪያ በሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡*

**16. Effective date of the Directive**

This Directive shall be effect from the date of signing by the Minister on 18 August 2021.

አዲስ አበባ

ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)

የሠራኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር

Addis Ababa

Ergogie Tesfaye (PhD)

Minister of

The Ministry of Labour and Social Affairs